# ቅንጅት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማሕበር

**KINIJIT** NORTH AMERICA ASSOCIATION OF SUPPORT **ORGANIZATIONS**
**(KNAASO)**
766 Rock Creek Church Rd. NW Washington DC. 20010
Tel: (202) 541 0556 Fax: (202) 541-0557 Email: kinijitna@kinijitna.org

## መግለጫ

## "አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ"

ይህ ስም የቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ መጠሪያ እንዲሆን መመረጡን የሰማነው በታላቅ ደስታ ነው። አዲሱ ስም ፀንቶ የቆየውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ምኞትና የቅንጅትን የማይናወጽ ዓላማ እንደገና አጉልቶ የሚያመላክት ስለሆነ በ1997 ምርጫ ዘመን ከዳር እስከዳር ተዘርቶ የነበረው የአንድነት፤ የዲሞክራሲና የመብት ተስፋ ተሀድሶ እንደሚያገኝ እምነታችን ጽኑ ነው።

ቅንጅት ስሙን እንዲለውጥ የተገደደው መንግሥት ባካሄደው ኢፍትሐዊ ተጽዕኖና አስተዛዛቢ ሤራ እንደሆነ እንኳንስ የኢትዮጵያ ሕዝብ እጽዋቱና አራዊቱ ጭምር የሚያውቁት ያደባባይ ምስጢር ነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ቅንጅትን የሚደግፈው ስለአርማው ሳይሆን ስለዓላማው ነውና በመጠሪያ "ይገባኛል አይገባህም" እንካ ሰላንቲያ ውስጥ ተጠምዶ ከትግሉ ሜዳ እንዲገለል መንግሥት ባዘጋጀው ወጥመድ ውስጥ ላለመግባት የፓቲው አመራር የወሰደውን ርምጃ እናደንቃለን። በወደፊቱ ተስፋ ላይ ያተኮረ ትግል ለማካሄድ ቃል ከገባና ከ "ይቻላል!" ዘመን ፓርቲ የሚጠበቀውም ይኸው ነው።

ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ለኢትዮጵያ መንግሥት ልናስገነዝብ የምንፈልገው ቁም ነገር አለ። ቅንጅት የሚሊዮኖች ራዕይ የተገለጸበት ፖለቲካዊና ማህበራዊ ክስተት እንጅ መንግሥትና ደጋፊዎቹ በየዋህነት እንደሚመኙት ብልጭ ብሎ ድርግም የሚል እንቅስቃሴ አለመሆኑን ነው። አዲሱ <u>"አንድነት ለዲሞክራሲና ለፍትሕ ፓርቲ"</u> የሚቀጥለው ይህንኑ ብሔራዊ ራዕይ አንዳነገበና የሚሊዮኖችን ድጋፍ እንደተጎናጸፈ ይሆናል። ይህ ፓርቲ ሠላም፤ ዲሞክራሲና በእኩልነት ላይ የተመሠረተ አንድነት የሰፈነባት ኢትዮጵያን በሠላማዊ መንገድ ለመገንባት በሚደረግ ጥረት ውስጥ የበኩሉን አደራ ለመወጣት ቃል ኪዳን የገባ ድርጅት ስለሆነ ይህን ታሪካዊ ግዴታውን እንዳይወጣ መንግሥት በሚወስዳቸው መሰናክሎች ለሚከተል መዘዝ ከተጠያቂነት እንደማይድን እናስገነዝባለን።

ሰሜን አሜሪካ የምንገኝ የድጋፍ ድርጅቶችና መላው ሕብረተሰብ የዴሞክራሲ ትግሉን መቀጠል ይቻል ዘንድ የቅንጅት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የስም ለውጥ ለማድረግ የወሰደውን እርምጃ ከልብ እንደግፋለን። ለቀጣዩ ትግል አስፈላጊ የሆኑትን ድጋፎች በአዲስ መንፈስ ተነሳስተን እንደምንቀጥል እናረጋግጣለን።

**ቅንጅት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማሕበር**
**ማርች 9 ቀን 2008 ዓ/ም**